# የኮሮና ቫይረስ (የኮቪድ-19) በሽታ ምላሽ አሰጣጥን አስመልክቶ የተዘጋጀ መግለጫ

ባለፉት 24 ሰዓት ውስጥ በተደረገው 3580 የላብራቶሪ ምርመራ ዘጠኝ (9) ሰዎች የኮሮና ቫይረስ ተገኝቶባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ በሀገራችን ቫይረሱ በምርመራ የተገኘባቸው ሰዎች ቁጥር ሁለት መቶ ሰባ ሁለት (272) ደርሷል፡፡ ቫይረሱ በምርመራ የተገኘባቸው ሰዎች ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ሲሆኑ 5 ወንድ እና 4 ሴት እንዲሁም እድሜያቸው ከ17 እስከ 66 ዓመት የሆኑ ናቸው፡፡ ቫይረሱ በምርመራ የተገኘባቸው 5 ሰዎች ከአዲስ አበባ ሲሆኑ፣ 4 ሰዎች ከሶማሌ ክልል (ጅግጅጋ ለይቶ ማቆያ) ይገኛሉ፡፡

የዕለቱ ታማሚዎች የተጋላጭነት ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

| **የተጋላጭነት ሁኔታ** | **የታማሚዎች ቁጥር** |
|---|---|
| የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ ያላቸው | 4 |
| በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ግንኙነት ያላቸው | 3 |
| የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ እና በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ግንኙነት የሌላቸው | 2 |
| ድምር | 9 |

## በሀገራችን የኮሮና ቫይረስ የሁኔታ መግለጫ

| | |
|---|---|
| አጠቃላይ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 45,278 |
| በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 3,580 |
| በዛሬው ዕለት በበሽታ መያዛቸው በላብራቶሪ የተረጋገጠ | 9 |
| በአጠቃላይ በቫይረሱ ተይዘው በለይቶ ከህክምና ውስጥ ያሉ | 157 |
| በፅኑ ህክምና ላይ ያሉ | 0 |
| አዲስ ያገገሙ | 0 |
| በአጠቃላይ ያገገሙ | 108 |
| በበሽታው ሕይወታቸው ያለፈ | 5 |
| ወደ ሀገራቸው የተመለሱ | 2 |
| እስከ አሁን ድረስ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር | 272 |

የላብራቶሪ ምርመራ ናሙናዎች ከተለያዩ ይበልጥ ተጋላጭ ከሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ ከጤና ተቋማት፣ በቫይረሱ ከተያዘ ሰው ጋር የቅርብ ንክኪ ካላቸው ሰዎች እንዲሁም በአስገዳጅ ለይቶ ማቆያ ውስጥ ካሉ ሰዎች ተወስዶ የተከናወነ ነው፡፡

የጤና ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የኮሮና ቫይረስ ሥርጭት መጨመርን ከግንዛቤ በማስገባት ሕብረተሰቡ ጥንቃቄዎችን አዘውትሮ እንዲተገብር ያሳስባሉ። በበሽታው መያዛችን ዕለት-ተዕለት በምናደርገው እያንዳንዱ እንቅስቃሴ የሚወሰን መሆኑን በማስታወስ የኮሮና ቫይረስ መከላከያ አራቱን የ"መ" ህጎች ተግባራዊ በማድረግ የበሽታውን ስርጭት እንድንከላከል በጥብቅ እናሳስባለን።

- **መራራቅ፡** አካላዊ ርቀት መጠበቅ፣
- **መታጠብ፡** እጅን በተደጋጋሚ በውሃና በሳሙና መታጠብ፣
- **መቆየት፡** አስገድጅ ካልሆነ ቤት ውስጥ መቆየት እንዲሁም
- **መሸፈን፡** ከቤታችን ወጥተን ስንቀሳቀስ የአፍንና የአፍንጫ መሸፈኛ (የፊት ማስክ) መጠቀም

በማንኛውም ሰዓት ጥቆማ ለመስጠትና መረጃ ለማግኘት እንዲሁም በቫይረሱ መያዛቸው ከተረጋገጡ ሰዎች ጋር የቅርብ ንክኪ ያላቸው ግለሰቦች ሪፖርት ለማድረግ በነፃ የስልክ መስመር 8335 ወይም በ952 ወይም በመደበኛ የስልክ ቁጥር 0118276796 በመደወል ወይም በኢሜል አድራሻችን ephieoc@gmail.com በመጠቀም ወይም ባሉበት ክልል በተዘጋጁ ነፃ የስልክ መስመሮች በመደወል ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በአካባቢው ለሚገኙ ጤና ተቋማት በስልክ እንዲያሳውቁ እንጠይቃለን።

ዶ/ር ሊያ ታደሰ
የጤና ሚኒስትር
ግንቦት 6፣ 2012 ዓ.ም